


**የተከበሩ አቶ ኤልማር ማማድያሮቭ**
**የአዛርባጃን ሪፐብሊክ ውጭ ጉዳይ ሚኒስተር**

# መልዕክት ከአዛርባጃን ሪፐብሊክ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

**የተከበራችሁ የ“IRS - ቅርስ” አንባቢያን**

ይህን ”IRS-ቅርስ” የተሰኘ እና በአማርኛ ቋንቋ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀ ልዩ እትም እንድታነቡ ስጋብዛችሁ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል። ቅርስ-Heritage መጽሄት የአዛርባጃንን ባህላዊ ቅርሶች በውጭ ሃገር ለማስተዋወቅ ያለመ ነው። መጽሄቱ በእንግሊዝኛ፣ ሩሲያኛ፣ ጀርመንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ አረብኛ፣ ጃፓንኛ፣ ቻይንኛ፣ ጣሊያንኛ፣ እና ስፔንኛ ቋንቋዎች የሚታተም ሲሆን ይህ ለኢትዮጵያውያን የታሰበው ልዩ እትም እውን በመሆኑ ደስታዬ ወደር የለውም።

በመጀመሪያ ይህ ልዩ እትም አዛርባጃን ሪፑብሊክ ነጻነቷን መልሳ የተቀዳጀችበትን 25ኛ ዓመት ክብረ-በዓል ምክንያት በማደረግ የተዘጋጀ ነው። ሁላችሁም እንደምታውቁት አዛርባጃን ሪፑብሊክ ነጻነቷን መልሳ የተቀዳጀችው የሶቪዬት ህብረትን ውድቀት ተከትሎ እ.ኤ.አ በጥቅምት 18/1991 ነው።

በ2017 የአዘርባጃን ሪፑብሊክንና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክን ድንቅ ግንኙነት እንደምናከብር ስነግራችሁ ታላቅ ኩራት ይሰማኛል። ሃገሮቻችን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የጀመሩት እኤአ ህዳር2/1992 ዓ.ም ነው። በእነኝህ ዓመታት ግንኙነታችን በሁሉም ዘርፎች ቀስበቀስ እያደገ መጥቷል።

እዚህ ላይ ለሁለቱ ሃገራት ግንኙነት መሰረቱ የተጣለው አዛርባጃን ነጻነቷን ከማግኘቷ ቀደም ብሎ መሆኑን መጥቀስ ግድ ይላል። በሶቪዬት አገዛዝ ጊዜ ወደ 800 የሚጠጉ ኢትዮጵያዊያን አዛርባጃን ውስጥ በሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች ተምረው የተመረቁ ሲሆን እነኝህ ምሩቃን በኢትዮጵያ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ክንውኖች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ እንደሆነ ይታወቃል።

የአዛርባጃን ኤምባሲ አዲስ አበባ ውስጥ መከፈት ሃገራችን ከኢትዮጵያ ጋር ያላት ግንኙነት ለማጠናከር ያላትን ከፍተኛ ቁርጠኝነት የሚያሳይ መሆኑን ልብ እንድትሉልኝ እፈልጋለሁ። ይህ የአዛርባጃን ውሳኔ ወሳኝ ከሆኑ ጥቂት የአፍሪካ ሃገራት መካከል ከምትመደበው ኢትዮጵያ ጋር ያላትን ትብብር እንዲጨምርም ያደርጋል።

ውድ አንባቢያን

በመጽሄቱ ላይ ጠንከር ያሉ ርእሰ ጉዳዮችንና እጅግ የተዋቡ ፎቶዎችን እንደምታገኙ እና እጅግ አስደናቂ የሆነችውን ሃገራችንን ለማዎቅ እንደምትችሉ እተማመናለሁ።

